# የዛሬ ሺህ አመት በአሁኑ ሰዓት፤
# እነማን ይሆኑ እዚህ ሚኖሩት?

ትኖር እንደሆነ    እናት ኢትዮጵያ፤
የነጻነት ቀንዲል    የታጋይ መለያ፤
ትኖር እንደሆነ    ኢትዮጵያ እናቴ፤
የእኔነቴ እትብት    አርማና ህይወቴ።

ትኖር እንደሆነ    ወሰኗን ጠብቃ፤
ሳይሸፍናት ፊቷን    በነገ ተጨንቃ፤
ትኖር እንደሆነ    ያላንዳች ጥያቄ፤
ሳይኖርበት ውስጧ    መራራ እስቄ።

የእኔነቴ ትክል    የህይወቴ ማማ፤
ትኖር እንደሆነ    በዘመን ተከርማ፤
ለጠላት ለወዳጅ    ሆና የህብር ዜማ፤

የመኖርሽ ሩህ    ሲጠፈነግ በጠማማ፤
ሲጨልም እኔነትሽ    መገነዝሽ ሲሰማ፤
ሲያላሉት ሲፈታቱት    የህብርሽን ካስማ፤
ሲያደቡ ሊጨፍሩ    በሞትሽ ዋዜማ፤

አትሆኚ እንደሁ    ይነገረኝ፤
በአጥፊ ጎጂ    በአማሳኝ፤
ተጎሳቁለሽ    ሆነሽ ብናኝ፤
በሌለበት    አልቃሽ አዛኝ።

ከሆነ    የማትኖሪ፤
ተመዝግብሽ    ሆነሽ ቀሪ፤
ያለ አዛኝ    ተቆርቋሪ፤
ያለህዝብ    ያለመሪ።

በእልፍ ዓመቱ    በዳግም ልደቱ፤
የእኔነትሽ ድግር    የመኖር እትብቱ፤
የፈጣሪሽ ፍቅር    ነግሶብሽ ምህረቱ፤
ትኖሪ ካለሆነ    በጊዜው በወቅቱ።

የማትኖሪ ከሆነማ    በአፍሪካ ካርታ፤
የማትሰለፊ ከሆነማ    ከጓደኞችሽ ተርታ፤
ፊትሽ ካልፈካ ማ    ተሞልቶ በደስታ፤

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ልሳንሽ ከተዘጋ    በእሪታና ዋይታ፤
ህዝብሽ ከላገኛ    ሰላምና እፎይታ፤
ምን ይፈይደናል    ጭፈራና እስክስታ፤
መቆዘም ሲገባን    በለቅሶና እሪታ።

እንግዲያማ!!

የእልፍ ዓመቱ ዋዜማ    ከታጀበ ሞቱ፤
ልፋት ድካማችን    ከሆነብን ከንቱ፤
ማንን ደስ ይለዋል    ሲጨፈር ማየቱ፤
ተገዝነሽ ስትሞች    በምእተ አመቱ፤
አፈርሽን ስትለበሽ    በአይን መመልከቱ።

ግና ደግሞ    ቅር አይለኝም እማማ፤
ለአንቺ እድገት    ብኳትን ብለፋማ፤
አውልቄ ብጥለው    ያን ድቅድቅ ጨለማ።

የምትኖሪልኝ ከሆነማ!
ቃል ልግባልሽ እማማ!

እርም ይሁንብኝ    ላልክድሽ ፈጽሞ፤
ኮሶ ይሁንብኝ    መራራ ቀጨሞ፤
ህይወቴም ቢሰዋ    ስጋዬም ቢደማ፤
ጉልበቴና እውቀቴ    ቢነድ እንደሻማ፤
ቆዳዬ ተገፎ    ቢለወጥ በጫማ።
ቅር አይለኝም    እማማ።

ግና ቅር ይለኛል    አገሬ፤
የእነነቴ መገለጫ    ማህደሬ፤
የታሪኬ ነጸብራቅ    ሚስጥሬ፤
ሆነሽ ከቀረሽ    ጠፍ እዳሪ።

ቅር ይለኛል    እማማ፤
ልጆቻችን የማይኖሩ    ከሆነማ፤
ካበቀልሽ ኩርንችት    አቃቅማ፤
ሆነሽ ከቀረሽ    ባድማ።

የእልፍ ዓመቱ    የጭፈራ ቀመር፤
የሁከት ጸጥታ    ቅይጥ ድምር፤
የተስፋ ቢስ እምነት    ውሁድ ድምር፤
የቀጺበ ተስፋ    ጥቅል ክምር፤

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ከገዘፈ ጽልመቱ ከጠይመ ቀናቱ፣
ከተፈተነ እምነቱ የመኖር የአንድነቱ፣
ከላላ መቋጠሪያው የህዝብሽ ውል ጽናቱ፣
ከሆነ መገለጫው የመሞትሽ እርገቱ፣
የእልፍ አእላፍሽ መቀበሪያ ማንነቱ።

የሚያጠላብሽ ከሆነ ተስፋሽ ከደመነ፣
ዕድልሽ ከጠመመ ከጠነነ ከጎፈነነ፣
መበታተንሽ ከቀጠለ ከፈጠነ ከፋነነ፣
ሁሉም በቄየው ከወገነ ከዘመነ።

ይቅርብኝ የኔ እማማ፣
መሬትሽ ከሆነ የማይለማ፣
ለምንስ ልልፋ ለምንስ ልድማ?
ደሜስ ለምን ይፍሰስ? የማይሆን ከሆነማ፣
የሚያጠላብሽ ከሆነ የጽልመት ሽማ፣
የሚሸፍን የሚያጨልም የእኔነትሽን አርማ፣
የሚያላብሱሽ ከሆነ ድቅድቁን ጨለማ፣
ሰንገውና አንቀው የህይወትሽን ዜማ፣
ልሳንሽን ቀፍድደው በቀረርቶ በግምገማ፣
ይቅርብኝ ድካሜ የልፋቴ ደማ፣

ይቅርብኝ እማማ!!

አልቆጠር በዜግነት ከህሊና ቢስ ጠማማ፣
ይቅርብኝ አልክፈል የደም ዋጋ ለአንቺ ጉማ፣
አልቆጠር ይቅርብኝ በእኔነቱ ካበጠ አፈ ጮማ፣
የማይታክት ለመተወን አንቺን በማጥፋት ድራማ።

ይቅርብኝ እማማ አልቆጠር በዜግነት፣
እኔነቴ ይቀበር አልታወስ በወራትና ዓመት።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com